**GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLOMBIA**

**Office of the Chief Financial Officer**

**Office of Tax and Revenue**

ቀን፡ አገስት 22 2008

ለ፡ ሁሉም የዲሲ የሲጋራ ጅምላ ሻጮች

ጉዳይ፡ የሲጋራ የኤክሳይስ ታክስ ጭማሪ

ቡሌቲን #፡ 2008 — 08

ከኦክቶበር 1, 2008 ጀምሮ የዲስሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሲጋራን ኤክሳይስ ቀረጥ መጠን ከፍ ያደርገዋል። ይህም አንድ 20 ሲጋራዎችን የያዘ ፓኮ ከ$1.00 ወደ $2.00 እንዲሁም አንድ 25 ሲጋራዎችን የያዘ ፓኮ ከ $1.25 ወደ $2.50 ሲሆን ይህም በ ዲሲ ኮድ ሴክሽን 47-2402(a) እንደተገልጸው ነው። አዲሱ የኤክሳይስ ቀረጥ ክፍያ የሚመለከተው አስቀድሞ ማህተም የተደርገባቸውን የፍሎር ስቶኮች ይመለከታል። እንዲሁም በ ዲ.ሲ. በጅምላ ሻጮች እና ቸርቻሪዎች ለንግድ ማከፋፈል ወይም ለሽያጭ የተያዙትን በቬንዲንግ ማሺን ውስጥ ያሉትን ሲጋራዎችንና ሁሉንም ማህተም የተደርገባቸውን ሲጋራዎችን ያጠቃልላል።

በኦክቶበር 1, 2008 የንግድ ስራ ከመጀመርዎ አስቀድመው በስቶክ ውስጥ ያልዎትን የዲሲ ማህተም ያለባቸውን ሲጋራዎችንና /ወይም በስቶክ ውስጥ ያሉትን ሉዝ ታክስ ስታምፕ የንብረት ቆጠራ(ፊዚካል ኢንቬንተሪ) ማድረግ ያስፈልግዎታል። ይህም የፍሎር ታክስዎን ለመወሰን ነው። በውስጡም የፍሎር ታክስ ሪተርን እንዲሁም መምሪያዎች አሉት። ተመላሹንና ክፍያውን እስከ ኦክቶበር 1, 2008 ድረስ ወደ Office of Tax and Revenue, Audit Division, Cigarette Tax Enforcement Unit, P.O. Box 556, Washington, DC 20044.ይላኩት። የወለል ቀረጥን (ፍሎር ታክስ) ሪተርን ፋይል ካላደረጉና እስከ ኦክቶበር 21 2008 ድረስ ካልተከፈለ በወንጀለኛነት ሊያስከስስዎት ይችላል። በተጨማሪ ምእራፍ 24ን ወይም በዚህ ምእራፍ ላይ የተደነገጉትን መተዳደሪዎች በመጣስዎ ምክኒያት (D.C. Code, 2001 Ed. 47-2404(f) & 47-2422(a)) የያዙት የሲጋራ ላይሰንስ(ፍቃድ) ሊታገድብዎት ወይም ሊሰርዝብዎት ይችላል።

የኦፊስ ኦፍ ታክስ ኤንድ ረቨኑ፣ የኦዲት ክፍል በተመረጡ የዲሲ የስራ ፍቃድ ያላቸው ጅምላ ሻጮች ላይ በኦክቶበር 1, 2008 ወይም ከዚያ በፊት የፊዚካል ኢንቬንተሪ(ቆጠራ) ማድረግ ይመርጥ ይሆናል። ከተመረጡ በኦዲት ዲቪዥርን ተወካይ አስቀድሞ የነገርዎታል።

የአዲሱ ስሌት የሲጋራ ታክስ ስታምፖስ ሮሎች ወይም ሽቶች ከዲስሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ኦፊስ ኦፍ ፋይናንስ ኤንድ ትሬዠሪ ከሴፕቴምበር 15, 2008 ጀምሮ መግዛት ይቻላል። ከዚህ ቀን በፊት መሸጥ የለበትም።የዲሲ የሲጋራ ቀረጥ ህግ እነዚህን ህጎች በሚጥሱ ላይ እርምጃ ይወስዳል። የተበላሹና "አሮጌ ማህተም" ያለባቸውን መሸጥ የሌለባቸው ሲጋራዎች ወደ ሲጋራ አምራቹ ከሴፕቴምበር 30, 2008 አስቀድሞ መመለስ ያስፈልጋል። ይህም ከዲሲ ትሬዠሪ ክሬዲት ለመቀበል ያስችላል።

በዚህ ማስታወቂያ ወስጥ ስለ ሲጋራ ፍሎር ታክስ ተዘውትረው የሚጠይቁ ጥያቄዎች(ተ.የ.ጥ.) ሽት አቅርበናል። የዚህ ማስታወቂያ ቅጂና ተ.የ.ጥ.(የተለያዩ ትርጓሜዎች) በዌብሳይታችን ላይ በ www.taxpayerservicecenter.com ይገኛል።

በተጨማሪም ዌብሳይታችን ስለ ፍሎርታክስ ሪተርንና መምሪያዎች አሉት። ስለዚህ ህግ መቀየር በተመለከተ ጥያቄዎች ካልዎት ወደ ኦፊስ ኦፍ ታክስ ኤንድ ረቨኑ, ኦዲት ዲቪዠን በ(202) 442-6602 ይደውሉ።

ለትብብርዎ እናመሰግናለን።